# እርር ድብን በሉ።

የብዙኃን ማህበርን ከመበጥበጥ፤
ደግፉኝ እያላችሁ ከመልመጥመጥ፤
ዲሲ አትላንታ ቺካግ ከመንከራተት፤
ሐሞታችሁ ፈሶ ከዚህ ከዛ ከመራወጥ፤
ይሻላል መጋባት ከወያኔ ረኸጥ።

እርር ድብን በሉ።
ራሳችሁን መቻል አቅቷችሁ ከመንከራተት፤
ቱልቱላ ከመንፋት ለበለጠ ውርደት፤
ደባ ብታድቡ ተንኮል ወይም ክፋት፤
ተገን አድርጋችሁ የፈጠራን ክህደት፤
እርዳታ አይገኝም ለፈጠራ ውሸት።

እርር ድብን በሉ።
አጀንዳችሁ ቢቀየር ሁሌም ዕለት በዕለት፤
መርሆአችሁ ክፋት ውሸትና ቅጥፈት፤
ከእበላባይ ማበር መሰለፍ ለስርቆት፤
ያከናንባችኋል አፍረትና ውርደት።

ታራላችሁ ትደብናላችሁ በቅናት በክስረት፤
ፍንክች አይል ኢህአፓ ከሐቅና ከእውነት፤
አይሰግድ አይከዳ አያሻሽጥ መሬት፤
ምንጊዜም ይሰዋል ለኢትዮጵያ ነፃነት።

ኢትዮጵያ በእውነተኛ ልጆቿ ነፃነቷን ትጎናጸፋለች
ከጎላ ምንጭ

በማሕበረ አንድነት(አትላንታ) ራድዮ ጣቢያ
ፀረ-ኢህአፓ ቃለ ምልልስ ምላሽ ትሆን ዘንድ የቀረበች ግጥም